# ዲያቆኑ እውን ኢትዮጵያን አያውቅ ይሆን?

ይነጋል በላቸው

የዴሞክራሲ አንዱና ትክክለኛው ገጽታ ሰው የመሰለውን በነጻነት መናገሩ ነው፡፡ ከዚህ አኳያ በድረ ገፆቻችን (የወቅቱ ብቸኛ የሃሳብ ማንሸራሸሪያዎቻችን) የምናደርገውን የሃሳብ ትግትግ በአወንታዊ መልኩ መቀበል ይኖርብናል፡፡ ሃሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት ደግሞ ማንም የማይሰጠን ወይ የማይነጥቀን ሊሆን ይገባል እንጂ አንድ ሰው እንደዬስሜቱ መርጦ እንደሚያዳምጠው ሙዚቃ መሆን የለበትም፡፡ ለዚህ ነው አንዳንድ ድረ ገፆች ላይ ቅሬታ እያደረብኝ እንዴት እንደማስረዳቸው እየጨነቀኝ ያለ፡፡ የመናገር ነጻነት ከሙዚቃ ምርጫ ጋር በጭራሽ አይገናኝም፡፡ አንድ ሰው መስማት የሚፈልገውን ብቻ ሊሰማ ከወደደ የሚሰማውን ነገር ስለማግኘቱ እጠራጠራለሁ፡፡ በዚህች በልዩነቶች ጡዘት በተወጠረች ዓለም ውስጥ ሁልጊዜ የሚጥመንንና የሚስማማንን ቅላጼ(ንግግር) ለማግኘት ማሰብ ሞኝነት ይመስለኛል፡፡ ቦታው የት ላይ ነው አትበሉኝና በመጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ የሚል ጥቅስ አለ፤ ‹ሰው ይህን አለኝ ብለህ አትቀየም፤ ምክንያቱም ከአንተ አፍ የሚወጡ ቃላትንም ልብ ብትል ብዙዎችን ስታስቀይም ትውላለህና፡፡› (ቃል በቃል አይደለም) አንድ ሰው ሌላው ቀርቶ ጧትና ማታ የሚያስበውና የሚናገረው እንኳን ይለያያል፡፡ ስለዚህ በመደማመጥና ተደማምጦ ሃሳብን በማንሸራሸር ሃሳብን በሃሳብ ማፋተግና ለመስማማት መሞከር፣ አለመስማማት ቢፈጠር ደግሞ በተለመደው አባባል እሱንም ቢሆን ላለመስማማት በጨዋነት መስማማት መጣር ይገባል እንጂ ዘወትር የሸሚዝ እጅጌ መሰብሰብና ጦርን መስበቅ ወይም በስድብ መሞላለጭ አግባብም ዘመናዊም አይደለም፡፡ ያ ዓይነቱ ከርሞ ጥጃነት መቅረት አለበት፡፡

አንድ ጸሐፊ ደግሞ የሰዎችን ስሜት ጠብቄ እጽፋለሁ ካለ ብዕር ዐይኗ ጠፋ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም የጸሐፊ ዘመድ የፖሊስ ዐመድ - ማነው - የቤንዚን ዐመድ የለውም ቢባል እውነት ነው፡፡ እነ እከሌን ለማስደሰት ወይም ለማስከፋት ተብሎ በቅድመ ዕውቅና ትንበያ የሚጻፍ መጣጥፍ፣ መጣጥፍ ሳይሆን የነገር ቁርሾ ማስተጋቢያ ነው፡፡ ጸሐፍት በመሠረቱ የሕዝብ ዐይንና ጆሮ ናቸው - ወይም ሊሆኑ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ስለሚጽፉት ነገር በተቻለ መጠን በቂ መረጃና ከተቻላቸው ደግሞ ማስረጃ ቢኖራቸው ይመረጣል፡፡ የሀገር ጉዳይ ሲነሳ እርግጥ ነው ብዙዎቻችን የስሜት ፈረስ እየጋለብን አልፎ አልፎ ከሰዎች ወይም ከቡድኖች ጋር የምንጋጭበት ጊዜ አለ፤ ያኔም ይህኛውን ወይም ያኛውን ቡድን ወይ አመለካከት የሚደግፉ ወይ የሚነቅፉ የሚዲያ አካላት ማዕቀባቸውን ይጥሉብናል - የሚሆነው ከመሆን ላይዘል ድከሙ ሲላቸው፡፡ የሆነው ይሁንና ታዲያ ስንጋጭና ብንጋጭም እንደተፈጥሯዊ አካሄድ በመውሰድ ሃሳብን በሃሳብ መቃወም ይገባል እንጂ የማያስፈልግ አታካራና ግላዊ እንካስላንትያ ውስጥ ገብተን ጠብን ማበራየት አያስፈልግም፡፡ ነውር ነው፡፡

በመግቢያነት እንደላይኛው ካልኩ ወደተነሳሁበት ጉዳይ ላምራ፡፡

ዲያቆን ሙሉጌታ የተባለ በድረ ገጾች አካባቢ የማውቀው ወገኔ ሰሞኑን በኢትዮሚዲያ ያወጣው ጽሑፍ ስሜቴን ማርኮታል፡፡ ይህ ጽሑፉ በሌሎች ላይ ገና አልወጣም ወይም አይወጣምም ይሆናል፡፡ ልኮ ከሆነ አለመውጣቱ እንደኔ ስህተት ነው፡፡ ‹ቤት ለእምቦሣ› ብሎ የኢሜይልን ‘inbox’ የሚያንኳኳን እንግዳ አልከፍትም ብሎ በደጅ ማባረር በጣም ትልቅ ስህተት ነውና የሚመለከታቸው ወገኖች ቢያስቡበት ጥሩ ነው - በቤቱ የሚኮራ ልጅና ምንትስ ናቸው ይባላል፡፡ እቤት ውስጥ እያሉ የሉም ማስባል ደግሞ ጨዋነት የሚጎድለው ከኢትዮጵያዊነት ትውፊትም ያፈነገጠ ጠባይ ነው፡፡ መቻቻልን ዛሬ ካልለመድነው መቼም አንለምደውምና ድረ ገፆች በምታምኑት ይሁንባችሁ እባካችሁን የማይጥማችሁንም ቢሆን አውጡትና አንባቢው ይፍረድ፤ ይነጋገርበት፤ ይማርበትም፡፡ ለምሳሌ የዲያቆኑን ጽሑፍ ባላነበው ስሜቴ ባልተነካና ብዕሬን ባላነሳሁ፡፡ ማንም በጻፈ ዓለም አታልፍም፤ እኔ የበሌ ልጅ ለምሳሌ ስንትና ስንት ነገር ጨንቁሬያለሁ - ግን ምን ለውጥ አመጣሁ? ምንም፡፡ ልፋትና ድካም ብቻ! ታዲያ ለምን ‹እምቢየው፣ አናወጣልህም› እባላለሁ?

ዲያቆን ሙሉጌታ በማስተባበልም፣ ለማግባባት በመሞከርም፣ በመስበክም፣ በማስጠንቀቅና በመዛትም መልክ የተነሳበትን ዓላማ ከዳር ለማድረስ ይሞክራል - ከመጣጥፉ መረዳት እንደቻልኩት፡፡ መነሻ ሃሳቡ - በፊት ቅቡ የሚታየው ስምምነትንና ሰላምን የመፍጠር ዓላማው ማለት ነው- እጅግ በጣም ሸጋ ነው፡፡ መነሻው ‹በኢትዮጵያ ውስጥ የትግሬ ገዢ መደብ ብሎ ቋንቋ የለም› ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሃሳቡ ውኃ ያነሳል ወይ? የክርስቶስን አባባል ልዋስና ይህ መነሻው የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እውነት አለው ወይ? በበኩሌ አንድን ሥጋት በግርድፉ ለማስወገድ ከመፈለግ የመነጨ የዋህነትን ታዝቤበታለሁ - ከጽሑፉ፡፡ ይህን እውነትን የተጠማ ጽሑፍ በማባረር ሳይሆን ተቀብሎ በማስተናገድና ተገቢውን መልስም በመስጠት ነው ለእውነት ንግሥና መቆም የሚቻለው፡፡ ስህተት በስህተት አይታረቅም፡፡ እንደብሂሉ ሁለት ስህተቶች አንድን ስህተት አያርሙትምና! [Two wrongs do not make a right.] ደግሞም ልቦች ከልብ ከተገናኙ የማይቃና ስህተት የለም፡፡ ችግራችን ባለመግባባት በሩቅ ሆነን ባገኘነው መሣሪያ (ለኛ ፈንጂና መትረየስ ቃላት) መጠዛጠዛችን ነው፡፡ ይሄኔ ሁላችንም ግማሽ መንገድ ተጉዘን መሃል ላይ ብንገናኝ ያጣላን የነበረው ነገር ሚዛን የማያነሣ ፍሬ ፈርስኪ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ትልቅ ሰው ደግሞ አጣን፤ አለቁብን ወይም ቀለሉብን ወይም አነሱብን፡፡ ታዲያ ከእኛው ትልቅ ሰው አናወጣም እንዴ? ጊዜ እኮ ሰው ይወልዳል፡፡ የጊዜ እንጂ የሰው ጀግና የለውም ያለው ማን ነበር ? የሚያጣላ እንጂ የሚያስታርቅ አጥተን ተመነቃቅረን እንቅር? ግን እስከ መቼ?

በኢትዮጵያ ምድር በጥቅም የተሳሰረ የጥቂት ግለሰቦች አንባገነናዊ አሰራር/ሥርዓት እንጅ የአንድ ብሔር/ክልል/ጎሳ የበላይነት ብሎ ነገር እንደሌለም አበክረን ልንተማመን ይገባል። "የትግራይ ገዢ መደብ" ብሎ ቋንቋ የለም! አለ ብሎ የሚያምን ግለሰብም ሆነ ድርጅት ቢኖር ግን የዚህ አካል ጥያቄ የሥርዓት ለውጥ ጥያቄ ሳይሆን ጠበንጃ የሚታጠቀው ለሌላ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ማንንም የማይበጅ ለብ ያለ አስተሳሰብና ጎደሎ ፖለቲካዊ አካሄድ ደግሞ ከዚህ ቀደም ግልጽ በሆነ ቋንቋ በተከታታይ ለመግለጽ እንደተሞከረ ያጠፋፉናል እንጅ ዓለም ወደ ደረሰችበት የስልጣኔ መንገድ አይቀላቅለንም። (መስመር ከራሴ)

ዲ/ን ሙሉጌታ ወልደገብርኤል E-mail yetdgnayalehe@gmail.com United States of America August 09, 2012

ይህ ከዚህ በላይ የተቀመጠው የዲያቆን ሙሉጌታ ሃሳብ በርግጥ እውነት ነው ወይ? ቢሆንልን በማን ዕድላችን! ግን ዋጮን ቢገለብጡት ያው ዋጮ ነው እንዲሉ ነው ነገሩ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ እኔ ራሴ ለብዙ ጊዜ እንደቁራ ጩሄበታለሁ - ኢትዮጵያ ውስጥ የትግራይ ገዢ መደብ ስለመኖሩ ወይም ሻል በሚል አገላለጽ ካለፉት 21 ዓመታት ወዲህ ይህ አስጠሊታ ግን ብንሸሸው እንኳን እንደጥላ በየሄድንበት እየተከተለ አሣራችንን እያበላን ያለው የትግራይ ገዢ መደብ የሚባል ነገር በጉልህ ስለመፈጠሩ፡፡ ቁስልን ቢሸፋፍኑት ይበልጥ ይነፈርቃል፤ መወሻሸትም እንደዚሁ ነው- አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ ይላል ገበሬው እንዲህ ያለ የመላላጥና የተጨፈኑ ላሞኛችሁ ዓይነት ነገር ሲገጥመው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በግልጽ ተወያይቶ መግባባት ያስፈልጋል፡፡ ወያኔ የአማራ ገዢ መደብ ነበር ብሎ ያምን የለም እንዴ? ታዲያ አሁን የትግሬ ገዢ መደብ አለ ቢባል እንደአካሄድ ምንድነው ነውሩ? የምን ማስተባበል ነው? ሀገሪቱን ከጫፍ እጫፍ አንቀጥቅጦ እየገዛት ያለው ከትግራይ የመጣ የመለስ ዜናዊ ምልምል መንጋ አይደለምና ነው ይሄ አገም ጠቀም ወንዝ የማያሻግር አመክንዮ ዛሬ የሚሰበከው? ‹አማራ ኢትዮጵያን አንቀጥቅጦ ገዝቶ› የትም አላደረሳትም፡፡ አየ መከራየ ስሸሸው የነበረው አሽሙሬ ሊመጣብኝ ነው መሰለኝ፡፡ አማራ ሲገዛ ምርጥ ምርጥ የሥልጣንና የጥቅም ቦታዎችን ሁሉ ለአማራዎች እየሰጠ፣ ለአማሮች ቆንጆ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ቀርፆ ለሌሎቹ ግን እንደሴክተር ሪቪው የጠላት ትውልድንና ሀገርን የመግደያ ሥልት ሥራ ላይ በማዋል አደድቦ በማይምነት ድቅድቅ ጨለማ እያሳወረ፣ የጦር ዕዙን ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በአማራ ጄኔራሎች እያስያዘ ሌሎቹን እንደባሪያ እረግጦ እያስደገደገ፣ የሀገሪቱን የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሙሉ በሙሉ በአማሮች አሲይዞ የሌላ ዘውግ አባላትን ለስደትና ለችግር እየዳረገ፣ … እንደነበረ የምናስታውሰው ነው፡፡ አሁን ደግሞ ዕድሜ ለትግራዩ ገዢ መደብ እኩልነትና ነጻነት በሀገራችን ምድር ከጫፍ እጫፍ - ከራስ ዳርጌ እስከ ራስ ዱሜራ ነግሦ ይሄውና ስደትና እንግልት ቆሞ፣ የንግዱና ኢንዱስትሪው ውጤት ለሁላችን እኩል ሆኖ በደስታና በፈንጠዝያ ላይ እንገኛለን፡፡ ሁሉንም ቢያወሩት ሆድ ባዶ ይቀራል፡፡ ለነገሩ ባዶ ያልሆነ ሆድ የት አለና! ዕድሜ ለወያኔ ጥቂቶች በቁንጣን፣ ብዙወች በጠኔ የሚጨነቁባት ኢትዮጵያ ተፈጥራለች፡፡

ዱሮ ማሽላና መሰሎቹ ብቻ ነበሩ እያረሩ የሚስቁ፡፡ ምነው ዲያቆን ሙሉጌታ? ምን አደረግሁህ? ማነው ያ አስቂኝ - ክበበው ገዳ - በዚያች የቄስን ባሕርይ ተላብሶ በቀላዳት ምርጥ ቀልዱ ‹ አይ ክበበው! እዚያ መድረክ ላይ ሥራ ፈቱን ሁላ የምታስቀው አንሶ እኔን እዚህ ልታስቀኝ መጣህ ?› እንዳለው ዓይነት ነው የሆነብኝ፡፡ ምን አስጨነቀህ ወንድም ዲያቆን? ትግሬ ገዢ መደብ ተባለ አልተባለ ምን አዲስ ነገር ይመጣ ብለህ? ስንትና ስንት ሌላ የሚጻፍበት ነገር ሞልቶ አሁን ይሄ አሳሳቢ ነገር ሆኖ ነውን? ወይም ዲያቆኑ ከኢትዮጵያ ከወጣ 21 ዓመት አልፎታል ማለት ነው፡፡ አንዳንዴ በውል የማያውቁት ነገር ሲያጋጥም ሰው መጠየቅ ወይም ጽሑፎችን ማገላበጥ ይገባል፡፡ እንጂ ኢትዮጵያ በአሁኑ ሰዓት በትግራይ ገዢ መደብ ብቻ ሳይሆን እየተገዛች ያለቸው ከትግራይና ከኤርትራ በፈለቁ፣ በነሱው ችሮታ የተገነጠለው ተገንጥሎ፣ የተሸጠው ተሸጦና ለጎረቤት ሀገር የተሰጠው ተሰጥቶ አሁን ኢትዮጵያ የሚሏትን ኢትዮጵያንም ዳር እስከ ዳር ባጥለቀለቁ፣ የውሸት ኢትዮጲያዊነትን ካባ ባጠለቁ፣ ሀገሪቷንና ሕዝቧን ለማጥፋት ተማምለው በተነሱ የትግራይ ወንበዴዎች እየተመዘበረች ናት፡፡ አይክፋህ ዲያቆን ሙሉጌታ፡፡ እውነቱ ይህና ይህ ብቻ ነው፡፡ ይህን የፈጠጠ እውነት ወዲታት ተጋሩም በሚገባ ያውቁታል፡፡ በኛም ላይ የወረደው በነሱም ላይ ወርዶ ለጊዜው የያዘ ይዞን እንጂ ፈጣሪ ፊቱን ሲመልስልን ሁላችንም የምንሠራውን እናውቃለን፡፡ ይህን እውነት መናገር ደግሞ አርማጌዶንን መጥራት አይደለም፤ አርማጌዶንን እዬጠሩ ያሉት ኢትዮጵያን እንደተምችና አንበጣ ከእግር እስከራሷ ወርረው እንደአልቅትና መዥገር ደሟን እዬማጉ፣ ሥጋዋን እዬጎመዱ፣ አጥንቷን እየጋጡ፣ መቅኒዋን በስሪንጋ እየመጠጡ ያሉት ባምቻና በጋብቻ እንዲሁም በዘርና በጎጥ የተሰባሰቡ የትግራይ ገዢ መደብ አባላት ናቸው፡፡ አገር ያወቀውንና ፀሐይ የሞቀውን እውነት ከማን ለመደበቅ ነው ይህ ሁሉ ዛቻ የተቀላቀለበት መስፈራርቻና ማስጠንቀቂያ ወንድማለም? ጥፊና ካልቾ ላይ ስድብ መጨመር ጉንጭን ማልፋት ነው ትርፉ ጎይታይ፡፡

እንዲህም ሲባል የትግራይ ሕዝብ አልፎለታል፤ ከዚህ ብሄራዊ ጭቆና ነጻ ነው፤ በሞሰኑ ልጆቹ ተጠቅሟል... ማለት እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡ አብረን ስለምንኖር እውነቱን እናውቀዋለን፡፡ ከዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር አንጻር ሕዝቡ እንደሕዝብ እንዲያውም ከእኛው ከመሰል ወንድምና እህቶቹ በበለጠ ተረግጦ እንደሚኖርም እናውቃለን- የዛሬውን አያድርገውና ነጻ ጋዜጣ እንኳን ለማንበብ እስከማይፈቀድለት ድረስ የተጨቆነ ሕዝብ ነው፡፡ እያልን ያለነው ታዲያ የጋራ ጠላትን በጋራ ታግለን የጋራ የሆነ - ለሥልታዊ ጠቀሜታም ቢሆን - አንዱን ወርቅ ሌላውን ጨርቅ የማያደርግ ሥርዓት እንፍጠር ነው፡፡ አለበለዚያ በአፍ ጅዶ ብናለባብሰው እውነቱ ስንዝር አያፈናፍነንም፡፡ ይህ ጉዳይ የትግሬነትና የአማራነት ወይም የሌላነት ጉዳይ አይደለም - የክር ጉዳይ ነው - የማተብ፡፡ የሃይማኖት ጉዳይ ነው - የነፍስ፡፡ እንደ ኤቨረስትና ራስ ዳሽን ተራራዎች ዐይናችን ፊት ለፊት የተገተረን ሀገራዊ እውነታ - ለምንም ዓይነት ፖለቲካዊም ይሁን ሌላ ጠቀሜታ - ሸምጥጠን ብንክድ ስለእውነት ሃያ አራት ሰዓት የቆመ እግዚአብሔር በመካከላችን አለና ይታዘበናል - ኅሊናችን እንኳን ፈቃድ ላይ ቢሆን ፡፡ ‹የትግሬ ገዢ መደብ ብሎ ቋንቋ የለም የሚል ካለ ጭፍን ትግሬ ብቻ ነው ሊሆን የሚችል› ሲሉ የምሰማውን እዚህ ላይ ከቁብ ጥፌ ልናገረው አልፈልግም፡፡ ግን እንዲህ የሚል ሰው ማንም ይሁን ማን እውነቱን ማወቅ ከፈለገ ወደ ኢትዮጵያ ይምጣና ሥልጣኑ ሁላ በማን እንደተያዘ፣ ንግዱ ሁላ በማን እንደተያዘ፣ አየር መንገዱ በማን እንደተያዘ፣ ባንኩና ኢንሹራንሱ በማን እንደተያዘ፣ ፖለቲካው ሙሉ በሙሉ በነማን ቁጥጥር ሥር እንዳለ፣ መከላከያውና ፖሊሱ ስለላውም በማን እንደተያዘ፣ ምን አለፋችሁ ... ማን ነዋሪ ማን ደግሞ አኗኗሪ እንደሆነ በቀላሉ ይመልከት፡፡ የመላዋን ኢትዮጵያን ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ለሚመለከት የውጭ ታዛቢ ‹እንዴ ለመሆኑ ትግራይ ውስጥ ሰው ቀርቶ ይሆን?› ማለቱ አይቀርም፡፡ ታዲያ ለምን ይዋሻል? ለምን ዓይነት ፍጆታና ትርፍ? ዞሮ መመልከቻው አንገት ወዴት ጠፋ? ደግሞም የቤተ ልሔምን ምሥጢር ካወቀ የእምነት ሰው እንዲህ ይጠበቃል? ክርስቶስ ‹ሁሩ ወመሀሩ ውስተ ኩሉ አጽናፈ ምድር› ብሎ ደቀ መዛሙርቱን ወደዓለም ያሠማራቸው እኮ እውነትን እንዲገልጡ እንጂ ለሥጋቸው ወይም ለግል ዓላማቸው አድልተው የዲያቢሎስ አርድዕት እንዲሆኑ አይደለም፡፡ በጊዜ ንስሃ እንግባ ምዕመናን! አካሄዳችን አላማረኝም፡፡ ትግሬ እየገዛ አይደለም ማለት ምን ማለት ነው? ውይ መጥፎ ቃል ሊወጣኝ ነበር - ከከንፈሬ ላይ ያዝኩት፡፡ እሰይ እንኳን ያዝኩት! እላይ የተናገርኩትን ሊያስተሃቅርብኝ?... ይሄ እንደጤዘ ረግፎ በጊዜ ሂደት የሚያልፍ ክፉ ዘመን እንዴቱን ያህል ከፋፍሎናል ጃል? አዬ ሆድ ክፉ! የአንዲት እናት ልጆችን እንዲህ አቤልና ቃየል ያደረገን እኮ ይህ አንድ እንጀራ ነው፡፡ ‹አንድ እንጀራ ለኔ መስታውቴ ነሽ፤ ከቶ የስንቱን ፊት ታሳይኛለሽ› አለ ገበሬው በሥነ ቃሉ፡፡ ሆድ እንኳን በበስተኋላችን አልሆነ፡፡ ገፍትሮ ገደል ይከተን ነበር፡፡ በሆድ የተነዳ ግሪሣ በመለስ ዜናዊ ‹ቆራጥና ብልኀ› አመራር ከትግራይ ተነስቶ ኢትዮጵያን በዘርና በነገድ፣ በጎሣና በብሔር፣ በሃይማኖትና በድንበር፣ መነሻውና ትርጉሙ በማይገባን የቤተ ሙከራ ሥሪት የእራፊ ጨርቅ ባንዴራና በሀብት በንብረት በታትኖና ከፋፍሎ ያሻውን እያደረገ እያለ ‹የትግራይ ገዢ መደብ› የለም ይባልልኛል፡፡ ሞኙህን ፈልግ፣ ሂድናም ሌላህን ብላ እባክህን - በልጅነት ‘go and eat another’ የምንባባለው በአእምሮየ ውልብ አለብኝ፡፡

በነገራችን ላይ የትኛውም የገዢ መደብ ቢኖር ግድ የለኝም፡፡ የዝንጀሮና የጦጣ የገዢ መደብም ይኑር ከፈለገ፡፡ ያ እኔን አያስጨንቀኝም፡፡ የሚያሳስበኝ አገዛዙ ላይ ነው፡፡ ‹ግዛኝ፣ ግዛኝ ብለው ሊሸጡኝ ፈለገ› የሚባል ተረት አለ ልበል? አዎ፣ ወያኔዎችን የጠላሁት ትግሬ በመሆናቸው አይደለም፡፡ ወያኔዎችን የጠላኋቸው ሱቅ ውስጥ እንደገባ ሕጻን በዐይን ዐዋጅ ሁሉንም የሀገሪቷን ሀብትና ንብረት እንያዝ ብለው ካለሀፍረትና ካለ አንዳች ይሉኝታ በመያዛቸው አይደለም፡፡ ወያኔዎችን የጠላሁት በነሱና በሚፈልጉት የሌላ ሰው ጉሮሮ ጠጅና ብርንዶ እየሰደዱ በማይፈልጓቸው ሚሊዮኖች ጉሮሮ ግን አጥንትና ጋሬጣ የሚሰኩ ተንኮለኛና ያልዘሩትን

የሚያጭዱ ሰይጣናዊ ፍጡራን በመሆናቸው ነው፡፡ ሰው ያደርገዋል ተብሎ የማይታሰብ ወንጀልና ዕኩይ ድርጊት በኢትዮጵያውያን ላይ ስለፈጸሙና እየፈጸሙም በመሆናቸው ከጥቅም ተጋሪዎቻቸው በስተቀር ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር በደመኝነት ደረጃ የሚፈላለጉ ፀረ ኢትዮጵያና የባንዳና የመሠሪ ታሪካዊ ጠላቶቻችን ልዑካን ናቸው - ዕድሜያቸው የረዘመውም ለዚህ ነው - በርግጥ የኛም ዳተኝነትና የርስ በርስ ንቁሪያ ታክሎበት፡፡ ወያኔዎች የትግራይን ሕዝብ አይወክሉም የሚባለው ነገር ደግሞ በጣም አነጋጋሪ ነው፡፡ የማን ናቸው ታዲያ? ከሰማይ ወረዱ ወይንስ ከመሬት እንደ አሸን ፈሉ? እንኳን ትግራይን በጉልበታቸው ኢትዮጵያን ወክለው ከፍለን የማንጨርሰው ዕዳ ውስጥ እዬከተቱን አይደለምን? እንግዲያውስ እንኳን ትግራይን እኛንም የሚወክሉ የጋራ ማፈሪያ ልጆቻችን ናቸው፡፡ በቃ፡፡ የምን ማለባበስ ነው፡፡ በዚህ ንግግሬ የሚቀየም ካለ ከፈለገ ያኩርፈኝ፡፡ እንዴ፣ አልበዛም? ደግሞም ትግራይ በወያኔዎች አልለማችም ስለሚባለው ነገር ጥናት ቢጤ ማድረግ ያስፈልጋል፤ ለነገሩ መልማቷ የደስታችን እንጂ የመከፋታችን ምክንያት ሊሆን ስለማይችል ጥናቱም አስፈላጊ አይደለም፡፡ የጎዳን የርሷ መልማት ሳይሆን እርሷ ስትለማና እስክትለማ ያየነውና እያየን ያለነው አበሳ ነው፡፡ ይሄ ኤፈርት የሚሉት ጃውሳ ልጇ እያለላት ምን ትሆናለች ለነገሩማ፡፡ ማርያምን ሰው የሚወዳት ለምን እንደሆነ ሲጠየቅ ‹ከግንድ የሚያላጋ ክርስቶስ የሚባል ልጅ ስላላት ነው› እንደተባለው ነው ነገሩ፡፡ ይብላኝ እንጂ ለኔዎቹ ከርታታዎች አዘዞና ሐሙሲት፡፡ ምነው ያንድ ቀን ሥልጣን ባገኝሁ፤ ሐሙሲት ላይ አንድ ወፍጮ ቤት አስተክል ነበር፡፡ ሲሾም ያልበላ አይደል ነገሩ? በሬ ካራጁ… ይሄው ኑሮ ተብሎ እንኖራታለን፡፡ ኑሮ ካሉት ፍሪጅም ይሞቃል ይላሉ ያራዳ ልጆች ተረቱን ለውጠው፡፡ ዳሩ ምን ያልተለወጠ ነገር አለ፡፡

እግረ መንገዴን የብዕር ወዳጄ ቤልጂግ አሊ ሰሞኑን በጻፈው ላይ የተሰማኝን ልግለጽና ከባሕረ ሃሳቤ እየጨለፍኩ የማቀርበውን ማዕደ-ቅሬታ ወብሶት ወደመዘምዘሙ ልሂድ፡፡

ከፍ ሲል ለመግለጽ እንደሞከርኩት ሰው የመሰለውን መጻፉ ትክክልና ተገቢ ነው፡፡ መጠንቀቅ የሚኖርብን የምንጽፈው ነገር ምን ያህል ደርዝ ያለው ነው የሚለው ነው፡፡ እርግጥ ነው ከፍ ሲል እንደተገለጸው አንዳንዴ ዛር ከፈረስ እየሆንን ሰውን ማስቀየማችን የማይቀር ነው፡፡ ለአብነት ዲያቆን ሙሌ በዚህች ጦማሬ ሳቢያ የዘንባባ ዝንጣፊ ያቀርብልኛል የሚል የዋህነት የለኝም፡፡ በጥሞና ካየልኝ ግን አንዳች እውነታን መገንዘቡ አይቀርም ብዬ ማመን እፈልጋለሁ፡፡ ዋናው ቀናነት ነው፤ የተቃወምኩት ነገር እውነቱ ተሸፈነ ብዬ እንጂ ሙሌ የተናገራቸው ብዙ ልጨኛ ቁም ነገሮች አሉ - በጽሑፉ፡፡

የቤልጂግ አሊ ጽሑፍ አንጀት አርስ ነው፤ ሰው በወደደው ሲቆርብም ደስ ይላል፡፡ ቤልጂግ ግልጽና አካፋን አካፋ ማለት ጥሩ እንደሆነ የሚያምን ይመስላል፡፡ እኔም ሃሳቡን በሃሳብ ደረጃ እጋራዋለሁ - አካፋን አካፋ ማለትን፡፡ ግልጽነት መልካም ነገር ነውና፡፡

ነገር ግን አንዳንዴ አካፋን አካፋ ስንል ከጥንቃቄ ብዛት ወይም ጉድለት አካፋን ከአካፋነት በላይ ወይ በታች የማይመጥነው ስያሜና ባሕርይ እንዳንሰጠው ልንጠነቀቅ ይገባናል ብዬ አስባለሁ፡፡ አካፋን አካፋ ስንል የምንናገርበት ቋንቋና በቋንቋው ውስጥ የሚገኙ ቃላት ምርጫ ሊታሰብበት ይገባል፡፡ በመሠረቱ ቋንቋ ውስብስብ ነገር ነው፡፡ በሚነገር ነገር ውስጥ ተሸጉጦ የሚገኝ ያልተነገረ ግን ደግሞ በአንድምታዊ ቅኝት የሚታወቅ ንግግር አለ፡፡ በቋንቋ ጥናት paralanguage የሚባል ሙያዊ ቃል አለ፡፡ ስትናገር ከምታወጣቸው ቃላትና ሐረጋት ወይም ዐረፍተ ነገሮች ብቻ ሳይሆን ከአነጋገር ለዛህ ወይም የንግግር ዐውድና ድባብ የሚወሰድ የተለዬ ትርጉም ካለ በዚህ የቋንቋ ጥናት ይዳሰሳል፡፡ ከቃላት ድግግሞሽህና ከቃላት ምርጫህ አንባቢህ ወይ አድማጭህ የሚረዳው አንተ ግን ያላሰብከውም ያሰብከውም ያመለጠህም… ነገር ይኖራል - እነ የምላስ ወለምታና ዐይነ ውኃ እንዲሁም የስሜት ሁኔታና የሰውነት እንቅስቃሴ በዚህ ውስጥ ይካተታሉ - በቀጥታ በቃላት የማይነገርን ፍቺ የምናገኝበት መንገድ ነው ፡፡ ያኔ ‹አሃ! ይሄ ሰውዬ በዚህና በዚህ ረገድ ይህን ሰው ይወደዋል ወይም ይጠላዋል› የሚባልበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡

ስለዚህም በተለይ በአሁኑ የሀገራችን የተወሳሰበ ፖለቲካዊ ሁኔታ አንዱን በጭፍን ላለመደገፍ ወይም ሌላኛውን በጭፍን ላለመውደድ ጥንቃቄ ማድረጉ ቢያንስ ከትዝብት ለመዳንና ለሀገራችን ፖለቲካ የመቻቻልን ባህል ከመፍጠር አኳያ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡ እርግጥ ነው ብዙዎቻችን በብሶትና በተስፋ መቁረጥ በመከበባችን አንዳንዴ ስለምንለው ነገርና የምንለው ነገር ስለሚያስከትለው ውጤት ልብ አንል ይሆናል፡፡ ለዚህም ይመስላል አንዳንድ ጅምሮች ብቅ ከማለታቸው በሰላ ሂስ የምንጠርባቸው - አካሄዳቸውን በውል ለመቃኘት እንድንችል ገና ጥቂት ጊዜም ሳንሰጣቸውና ሳንታገሳቸው፡፡ እንዲህ ዳር ዳሩን መሄዴ ወድጄ አይደለም፡፡ በየመስመሮች መሀል ያነበብኩት ነገር ስላለኝ ነው -በቤልጂግ ጽሑፍ፡፡ ለምሳሌ አንዲት ቃል ከሦስት ጊዜ ባላነሰ በአላስፈላጊ ሁኔታ ተጠርታለች - ሆን ብዬ ተውኩት እንጂ አንገት አካባቢ የምትውል ነገር ናት ብዬ የቃሊቱን ምንነት ብጠቁም ደስ ባለኝ፡፡ ምን ትሠራለች ? የፈጠጠው እውነት ጎያው ምሥክር ሆኖ እያለ ያቺ ቃል ተደጋግማ መጠራቷና ስንትና ስንት በገሃድ የሚስተዋል ገመና እያለ ያቺን ነገር እየደጋገሙ ማንሳቱ ምን ፋይዳ አለው - የሰዎችን ስሜት ከማጎፍነን በስተቀር? ስለዚህ ይህ ዓይነቱ ጫፎችን እየወሰድን መተራረቡ ላልተወሰነ ጊዜ ቢቋረጥ - ከምንተቸው ነገር ብዙም የማይገናኙ ግላዊ ነገሮች በፊት ለፊት የጽሑፋችን ክፍል ላይ ሚዛን በሚደፉ መልክ ባይመጡ መልካም ነው - ሆድ ስንት ነገር ይችል የለ፡፡ ቢቻለን ሁላችንም ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ

ላለመወራረፍ ቃል ገብተን በገንቢ መስመር እየተባበርን የነጻነታችንን ዘመን ብናቃርብ ከሁሉ የበለጠው ውብ ነገር ነው፡፡ ያ ባይቻለን ደግሞ አንዳችን የአንዳችንን መጥፋት ሳንመኝና ሳንመቀኛኝ - ሰድቦ ለሰዳቢ እንዲሉ በከንቱም እየተሰዳደብን መናቆራችንን በጉጉት አሰፍስፎ ለሚጠባበቅ ሰዳቢ ሳንደራረግ - የየበኩላችንን ጥረት በየፊናችን አድርገን አንድ ማዕከላዊ ቦታ ብንገናኝ ከዚያም ፍርዱን ለሕዝቡ ብንሰጥ የተሻለ ነው ብቻ ሳይሆን እንደብቸኛ አማራጭ ብንወስድ የዳግም ልደት ያህል መታደል ነው፡፡ በድጋሚ ላስታውስ የምፈልገው ነገር ግን እባካችን እሚገናኙ እማይመስሉ  ጫፎችን እየያዝን ለያዥ ለገራዥ አናስቸግር፡፡  ያሳለፍነው ይብቃን፡፡ ወያኔን የመሰለ ጠላት ጎልቶ በከንቱ መወራከብ ጥቅሙ ለወያኔ ብቻ እንጂ ለእኛም ሆነ ለሀገራችን ድንቡሎ ትርፍ አያመጣም፡፡ ሰው እንዴት ዕድሜ ልኩን በነገር ዱላ እየተናቆረ ይኖራል?  አሁን እንኳን ወደስምምነት የጋራ መድረክ እንምጣ እንጂ፡፡ ወጡ ሳይወጠወጥ ምንድነው ይህ ሁሉ የቃላት ጦርነትና እሰጥ አገባ? ኧረ አቅል ጀባ!

ለፈቀደኝ አድራሻ አለኝ፡- yinegal3@gmail.com